መልእክት ዘጠኝ

## በእግዚአብሔር ክብር የተሞላው የእግዚአብሔር መቅደስ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ዘጸ. 24፡16፤ 40፡34-35፤ 1 ነገ. 8፡10-11፤
ሐዋ. 7፡2፣ 55፤ ዮሐ. 17፡22፤ ኤፌ. 3፡21፤ ራእ. 5፡13፤ 21፡9-11

**I. ክብር የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፤ ክብር የእግዚአብሔር መገለጥ፣ በግርማው የተገለጠ እግዚአብሔር ነው—ዘጸ. 24፡16፤ ሐዋ. 7፡55።**

**II. የእግዚአብሔር ክብር ማደሪያውን እና መቅደሱን ሞላ—ዘጸ. 40፡34-35፤ 1 ነገ. 8፡10-11፡-**

ሀ. "ደመናውም የመገናኛውን ድንኳን ከደነ፥ የእግዚአብሔርም ክብር ማደሪያውን ሞላ"—ዘጸ. 40፡34፡-

1. ማደሪያው በተተከለበት ቀን ደመናው በላዩ ላይ ወርዶ ጋረደው፣ የእግዚአብሔር ክብር ገብቶበት ማደሪያውን መሙላቱ ታላቅ ቀን ነበር—ቁ. 2፣ 34-35፡-

   ሀ. በማደሪያው ድንኳን ዙሪያ የተሰባሰቡት ደመናውን ማየት ችለዋል፣ በመጨረሻም ወደ ማደሪያው ቅድስተ ቅዱሳን የገባው ሊቀ ካህናቱ የማደሪያውን የውስጡን ክብር ማየት ችሎ ነበር—ዘሌ. 16፡15፤ ዕብ. 9፡7።

   ለ. ይህም የሚያመለክተው በእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ያለውን የእግዚአብሔር ክብር እንለማመድ ዘንድ በገበታው ላይ ኅብስቱን ለመደሰት እና የዕጣኑ መሠዊያ ጋር ለመማለድ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት ልምምዳችን ወደ ማደሪያው ድንኳን—እንደ የእግዚአብሔር አካል መልበስ ወደ ክርስቶስ—ወደ ፊት መገስገስ እንዳለብን ነው—ዘጸ. 40፡34-35፤ ዮሐ. 1፡14።

2. በደመና የተሸፈነው እና በክብር የተሞላው የማደሪያው ድንኳን ለእስራኤል ልጆች ትልቅ በረከት ነበር፣ ነገር ግን እነርሱ በምሳሌ ብቻ የነበራቸው እኛ ዛሬ እውነታው አለን—14፡2-3፣ 6፣ 10-11፣ 16-18፣ 20፣ 26፤ ኤፌ. 2፡18-22፤ 3፡16-21።

ለ. "የእግዚአብሔርም ክብር የእግዚአብሔርን ቤት ሞልቶ ነበር"—1 ነገ. 8፡11፡-

1. መቅደሱ፣ በምድር ላይ ብዙዎች የተካተቱበት የእግዚአብሔር መገለጥ እና ማደሪያ፣ በእግዚአብሔር ክብር ተሞልቶ ነበር—ቁ. 10-11።

2. በሰማያት ያለውን አምላክ ወደ ምድር በማምጣት እና ምድርን ከሰማያት ጋር በማጋጠም፣ የያህዌ ክብር የያህዌን መቅደስ ሞላው—ቁ. 11።

3. በዘፍጥት 28 ያዕቆብ "መሰላል በምድር ላይ ተተክሎ፥ ራሱም ወደ ሰማይ ደርሶ" ሕልም አለመ (ቁ. 12)፣ "ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ ሌላ አይደለም፤ ይህም የሰማይ ደጅ ነው" ብሎም ተናገረ (ቁ. 17)፡-

   ሀ. በዚያ ስፍራ ሰማይ ወደ ምድር ወረደ፣ ምድርም ከሰማይ ጋር በመሰላሉ ተጋጥሞ ነበር።

   ለ. ይህም መሰላል የክርስቶስ ምሳሌ ሲሆን እርሱም እንደ ሰው ልጅ በስብእናው፣ በምድር ላይ እንደ መሰላል የተተከለው እና ወደ ሰማይ የሚያመራው፣ ለእግዚአብሔር ቤት፣ ለቤቴል፣ ሰማይን ወደ ምድር ክፍት አድርጎ የሚጠብቀው እና ምድርን ከሰማይ ጋር ያጋጠመው ነው—ዮሐ. 1፡51፤ ዘፍ. 28፡19።

   ሐ. ዛሬ ሰማያዊው አምላክ ወደ ምድር ይወርዳል፣ ምድርም በውስጣችን በሚያድረው ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ጋር ተጋጥማለች—ቆላ. 1፡27።

   መ. እግዚአብሔር ከሰማይ ብቻ ሳይሆን የወረደው፣ ነገር ግን የእርሱ ሼካይና ክብርም መቅደሱን ሞላው—1 ነገ. 8፡10-11።

**III. ሦስታንዱ አምላክ የክብር አምላክ ነው—ሐዋ. 7፡2፣ 55፡-**

ሀ. እግዚአብሔር የክብር አምላክ ነው—ቁ. 2፣ 55፡-

1. እግዚአብሔር በሚገለጥበት ጊዜ ሁሉ፣ ያ ክብር ነው፤ የማይታየው አምላክ አምላክ ነው፤ የተገለጠው አምላክ ክብር ነው—ዘጸ. 13፡21።

2. የክብር አምላክ ለአብርሃም ተገለጠለት፣ ጠራው፣ ከዓለምም ለእግዚአብሔር ለየው፤ እርሱም ተስቦ በዚያ ክብር ተማረከ—ሐዋ. 7፡2።

ለ. በኤፌሶን 1፡17 ጳውሎስ *የክብር አባት* የሚለውን አገላለጽ ይጠቀማል፡-

1. የክብር አባት በብዙ ልጆቹ በኩል የተገለጠው አምላክ ነው—ዕብ. 2፡10።

2. *አባት* የሚለው መጠሪያ የሚያመለክተው ዳግም መወለድን ነው፣ *ክብር* የሚለው ቃል የሚያመለክተው መገለጥን ነው፤ ስለዚህ፣ *የክብር አባት* የሚለው መጠሪያ የሚያመለክተው ዳግም መወለድን እና መገለጥን ነው።

ሐ. ክርስቶስ ወልድ እና እግዚአብሔር አብ በክብር አንድ ዓይነት ናቸው—ዮሐ. 17፡5፡-

1. ክርስቶስ ወልድ የእግዚአብሔር ክብር መንጸባረቅ ነው፤ ወልድ የአብ ክብር ደምቆ መብራቱ፣ ብሩህነቱ ነው—ዕብ. 1፡3።
2. ክርስቶስ የክብር ንጉሥ፣ የሠራዊት (ማለትም፣ የሠራዊቶች) ጌታ እግዚአብሔር ነው ፣ የተጠናቀቀው ሦስታንዱ አምላክ ድል በነሣው እና በሚመጣው ክርስቶስ አካል ለብሷል—መዝ. 24፡7-10፤ ሉቃ. 21፡27፤ ማቴ. 25፡31።
3. ክርስቶስ የክብር ጌታ ነው—1 ቆሮ. 2፡7-8፡-

   ሀ. ክርስቶስ ዛሬ ሕይወታችን ነው፣ ለወደፊትም ክብራችን ነው—ቆላ. 3፡4፤ 1፡27።

   ለ. እግዚአብሔር ወደዚህ ክብር ጠርቶናል፣ ወደ ውስጡም እርሱ ያመጣናል—1 ጴጥ. 5፡10፤ ዕብ. 2፡10።

መ. አንደኛ ጴጥሮስ 4፡14 ስለ "የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ" ይናገራል፡-

1. የክብር መንፈስ የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።
2. የክብር መንፈስ ክርስቶስ በትንሣኤው የከበረበት መንፈስ ነው—ሮሜ 1፡4።
3. ይህ የክብር መንፈስ ራሱ ስደት ሲደርስባቸው ሳለ መከራን በሚቀበሉ አማኞች ላይ ያርፋል፣ ይህም አሁን በክብር ያለውን፣ ከሞት የተነሣውን እና ከፍ ከፍ ያለውን ክርስቶስ ለማክበር ነው—1 ጴጥ. 4፡13-14።

## IV. የእግዚአብሔር ክብር ውስጠ-መሠረታዊ በሆነ መልኩ ከእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ጋር የተገናኘ ነው —1 ጢሞ. 1፡4፤ ኤፌ. 1፡10፡-

ሀ. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ግብ ብዙዎች ለተካተቱበት ዘላለማዊ መገለጥ—ለአዲሲቱ ኢየሩሳሌም—ብዙ ልጆቹን ወደ ክብር ውስጥ ማምጣት ነው—ዕብ. 2፡10፤ 1 ቆሮ. 2፡7፤ ኤፌ. 1፡5-6፣ 12፣ 14፤ ራእ. 21፡7፣ 9-11።

ለ. እኛ እርሱን እንገልጥ ዘንድ እግዚአብሔር ክብሩን እንድናገኝ አስቀድሞ ወስኖናል፤ ስለዚህ፣ እግዚአብሔር እኛን አስቀድሞ የመወሰኑ ግብ የእኛ መከበር ነው—1 ቆሮ. 2፡7።

ሐ. ለክብር እንደ ተዘጋጁ የክብር ዕቃዎች እግዚአብሔር በመልኩ ፈጠረን፤ እኛ እርሱ በክብሩ የሆነውን ነገር እንገልጥ ዘንድ በእርሱ ሉዓላዊነት የእርሱ የክብር ዕቃዎች ለመሆን አስቀድመን ተወስነናል—ዘፍ. 1፡26፤ ሮሜ 9፡21፣ 23።

መ. የክርስቶስ ቤዛነት የእግዚአብሔርን የክብር ጥያቄ አሟልቷል—3፡23-25፤ ዕብ. 9፡5፤ ተዛ. ዘፍ. 3፡24።

ሠ. በእግዚአብሔር የክብር ወንጌል በኩል፣ እግዚአብሔር በዘላለማዊ ክብሩ እና ወደ ዘላላማዊ ክብሩ ውስጥ ጠርቶናል—2 ቆሮ. 4፡4፤ 1 ጢሞ. 1፡11፤ 1 ተሰ. 2፡12፤ 1 ጴጥ. 5፡10፤ 2 ጴጥ. 1፡3።

ረ. ሁሉን-ያካተተው ክርስቶስ እንደ የክብር ተስፋ በውስጣችን ይኖራል—ቆላ. 1፡27፤ 3፡4፣ 11።

ሰ. የጌታን ክብር ስንመለከት እና ስናንጸባርቅ፣ ወደ ጌታ መልክ ውስጥ ከክብር ወደ ክብር እየተለወጥን ነው—2 ቆሮ. 3፡18።

ሸ. እኛ በዘላለማዊ ክብሩ ውስጥ እንድንሳተፍ እና እንዲያውም የእግዚአብሔር ክብር እንድንሆን እግዚአብሔር አብ እንደ የጸጋ ሁሉ አምላክ በውስጣችን እየተንቀሳቀሰ ነው—1 ጴጥ. 5፡10።

ቀ. በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የእግዚአብሔር ክብር የመለኮታዊውን መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ የሚያካትት ነው—እግዚአብሔር ሰው መሆኑ ይህም ሰው በሕይወት፣ በባሕርይ እና በአገልግሎት ነገር ግን ተመላኪነቱን ሳይጨምር እግዚአብሐር ይሆን ዘንድ ነው—ዮሐ. 1፡14፤ ሮሜ 8፡3፤ 1፡3-4፤ ቆላ. 3፡4፤ ዕብ. 2፡10፤ ራእ. 21፡10-11።

## V. በዮሐንስ 17፡22 ጌታ ኢየሱስ፣ "እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ ...የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ" ብሎ ጸለየ፡-

ሀ. በዘላለማዊው ሕይወት ስላለው የአንድነት ደረጃዎች በአብ ስም ከጸለየ በኋላ (ቁ. 6-13) እና በቅዱሱ ቃል መቀደስ በኩል ስላለው የአንድነት ደረጃ ከጸለየ በኋላ (ቁ. 14-21)፣ ጌታ ስለ ሦስተኛው ደረጃ ማለትም ብዙዎች ለተካተቱበት ለሦስታንዱ አምላክ መገለጥ የአማኞች አንድነት በመለኮታዊው ክብር ውስጥ ይሆን ዘንድ ጸለየ (ቁ. 22-24)።

ለ. አብ ለወልድ የሰጠው ክብር በወልድ ለእኛ ስለተሰጠን እውነተኛው አንድነት ያለው በመለኮታዊው ክብር ውስጥ ነው—ቁ. 22፡-

1. ክብር አብን በሙላቱ ለመግለጥ ለወልድ ከአብ መለኮታዊ ሕይወት እና ባሕርይ ጋር በአብ የተሰጠው ልጅነት ነው—ቁ. 1፣ 5፣ 22።
2. አራት የክብር ገጽታዎች አሉ፡- ልጅነት፣ የአብ ሕይወት፣ የአብ መለኮታዊ ባሕርይ እና የአብ በሙላቱ የሆነ መገለጥ፤ እነዚህ አራት ነገሮች እኛ በወልድ ካለን ክብር ጋር እና በወልድ ከተሰጠን ክብር ጋር እኩል ናቸው—ኤፌ. 1፡5፤ 4፡18፤ 1 ዮሐ. 5፡12፤ 2 ጴጥ. 1፡4፤ ራእ. 21፡9-11።

ሐ. በሦስተኛው የአንድነት ደረጃ፣ አማኞች፣ እኔነታቸው ሙሉ በሙሉ ተከዶ፣ ፍጹም እንደ ተደረገው የአንድነታቸው መንስኤ የአብን ክብር ይደሰታሉ በዚህም በጋራ፣ በተገነባ መንገድ እግዚአብሔርን ይገልጡታል—ዮሐ. 17፡22፦

1. ጌታን ለማግለጥና ለማክበር ፍጹም በሆነ መንገድ ወደ አንድነት ውስጥ ፍጹማን የምንደረገው በሦስተኛው የአንድነት ደረጃ ብቻ ነው።
2. የእግዚአብሔር መታየት እና መገለጦች ለመሆን ዓለማ የእግዚአብሔር ሕይወት፣ ባሕርይ፣ እንዲያውም እግዚአብሔር ራሱ ይኖረናል—ቁ. 22።

**VI. በኤፌሶን 3፡21 ጳውሎስ፣ "ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን" በማለት ያውጃል፦**

ሀ. እንደ እግዚአብሔር ክብር ባለጠግነት መጠን ወደ ውስጡ ሰዎችን እንድንጠነክር እየተደረግን ነው፤ ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቅዱሳን ውስጥ መሠራት እንደሚችል ነው—ቁ. 16፤ 2 ቆሮ. 3፡18።

ለ. በኤፌሶን 3፡21 *ለእርሱ ክብር ይሁን* የሚለው የሚያመለክተው ወደ ቅዱሳን ውስጥ የተሠራው የእግዚአብሔር ክብር፣ ወደ እግዚአብሔር እንደሚመለስ ነው።

ሐ. ይህም ክብር ወደ እኛ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ጋር ነው፣ ወደ እኛ ውስጥም ከተሠራ በኋላ ወደ እግዚአብሔር የሚመለሰው ከእኛ ጋር ነው፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከብርበት መንገድ ይህ ነው—ቁ. 16-21።

መ. በዚህ የሁለት አቅጣጫ ምልልስ ቤተ ክርስቲያን፣ በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ እንደ በኩራት (ያዕ. 1፡18)፣ ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ቅድሚያውን ትወስዳለች፦

1. የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሠርቷል፣ እርሱም በቤተ ክርስቲያን ተገልጧል—ኤፌ. 1፡22-23፤ 2፡21-22፤ 3፡16-17፣ 19።
2. ለእግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ክብር ነው፤ ይህም ማለት፣ እግዚአብሔር የሚከብረው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ነው—ቁ. 21።
3. እግዚአብሔር የሚከብረው በዚህ ዘመን፣ በቤተ ክርስቲያን ዘመን ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በሚመጣው ዘመን፣ በመንግሥቱ ዘመን እና በዘላለም ዘመናት፣ ማለትም በዘላለም ውስጥም ነው—ማቴ. 6፡13፣ 29፤ ሮሜ 16፡27፤ ራእ. 5፡13፤ 21፡10-11።
4. እግዚአብሔር በዘመናት ሁሉ፣ ከአሁኑ ዘመን ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ፣ ይከብር ዘንድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና በክርስቶስ መክበር አለበት—ኤፌ. 3፡21።

**VII. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከሁሉ የላቀው ገጽታዋ የእግዚአብሔር ክብር፣ የእግዚአብሔር መገለጥ ያላት መሆኗ ነው—ራእ. 21፡11፣ 23፦**

ሀ. አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ ለዘላለም ብዙዎች እንደ ተካተቱባት የእግዚአብሔር መገለጥ፣ የእግዚአብሔር መልክ ያላት፣ በክብሩ የእግዚአብሔርን መልክ የምትገልጥ ናት—ቁ. 10-11; 4፡3።

ለ. መላዋ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ከተማ የእግዚአብሔርን ክብር የምትይዝ ናት፣ ይህም በመላዋ ከተማይቱ ውስጥ የሚያበራው እግዚአብሔር ራሱ ነው—21፡11፦

1. የእግዚአብሔር ክብር የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ይዘትዋ ነው፣ ምክንያቱም ከተማይቱ በክብሩ የተሞላች ናትና፤ ይህም የሚያመለክተው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም እግዚአብሔርን ለመያዝ የሆነች ዕቃ እና እርሱን የምትገልጥ መሆኗን ነው።
2. የእግዚአብሔር ክብር በእርግጥ እግዚአብሔር ራሱ መገለጡ ነው፤ ስለዚህ፣ ቅድስቲቱ ከተማ በእግዚአብሔር ክብር የተሞላች ትሆን ዘንድ እግዚአብሔር በዚች ከተማ ውስጥ ተገልጧል ማለት ነው።

ሐ. የእግዚአብሔር ክብር፣ የተገለጠው እግዚአብሔር፣ በኢያስጲድ ቅጥር በኩል በማብራት አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን እንድትበራ ያደርጋታል —ቁ. 23፣ 18፦

1. የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ብርሃን፣ ልክ እንደ ኢያስጲድ ድንጋይ፣ ልክ እንደ ብርሌ የጠራ ነው—ቁ. 11።
2. የእግዚአብሔር ክብር በበጉ በክርስቶስ በኩል ልክ እንደ መብራት በቅድስቲቱ ከተማ ቅጥር በኩል ያበራል—ቁ. 23፣ 18።

መ. እግዚአብሔር አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን ነው፣ እርሱን ማክበርም እርሱን እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መውሰድ እና ክብርን ሁሉ ለእርሱ መስጠት ነው—ቁ. 22፤ ሮሜ 15፡5-7፦

1. እግዚአብሔርን ማክበር በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሳተፍ ነው—ራእ. 3፡12፤ 21፡11።

2. እግዚአብሔር የእውነት በአጽናፍ ዓለም የሚከብረው እርሱን በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም ስንገልጥ ብቻ ነው—ሮሜ 16፡27፤ 1 ቆሮ. 10፡31።

ሠ. እንደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ ለእግዚአብሔር ክብር መወደስ እንሆናለን—ኤፌ. 1፡12፦

1. በዘላለም ውስጥ ሁሉም የእግዚአብሔር ልጆች ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ይሞላሉ፣ እግዚአብሔርንም ይገልጣሉ—ዕብ. 2፡10።
2. እግዚአብሔር በከበሩት ልጆቹ በኩል ይገለጣል፣ ይህም የተገለጠው እግዚአብሔር ክብር ነው—ራእ. 21፡7።
3. በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ ያሉት መላእክት እና አምንታዊ ነገሮች ሁሉ የተገለጠውን አምላክ ያወድሳሉ፤ ስለዚህ፣ እኛ፣ የከበርን የእግዚአብሔር ልጆች ለክብሩ መወደስ እንሆናለን—ኤፌ. 1፡12።

*© 2022 Living Stream Ministry*